# ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

ቅፅ ፩፣ ቁጥር ፫፣ ህዳር ፳፻፲፫ ዓ.ም

**ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ** በሚል ርዕስ በየሁለት ወሩ በአካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን እየተዘጋጀች የምትሰራጨው ይህቺ ዜና መፅሄት የኢትዮጵያን በፈቃደኛነት ላይ የተመሰረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖ ለመቀነስ የተዘጋጀውን ዕቅድና አፈፃፀሙን በተመለከተ መረጃዎችንና አዳዲስ እውቀቶችን ለተለያዩ ባለድርሻዎች የማድረስ ዓላማ አላት።



"ተፈጥሮን መሠረት ያደረጉ መፍትሄዎች የአየር ንብረት ለውጥን አውዳሚ ተፅዕኖዎች ለመግታት ቀዳሚ ምርጫዎቻችን ናቸው።"

ክቡር ፐ/ር ፍቃዱ በየነ የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ኮሚሽነር

## በዚህ እትም. . .


በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ ቅነሳን ለማሳካት የግብርና ዘርፉ ድርሻ ፪

ዜናዎች ፪

የኢትዮጵያ የከተሞች ደረቅ ቆሻሻ ዘርፍ ለብሄራዊ በፈቃደኛነት ላይ ለተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ ቅነሳ የሚያበረክተው ሚና ፯

ሁነቶች ፯

ልዩ ልዩ ህትመቶች ፺





**ዋና አዘጋጅ፡** ንጉሱ ለማ ገብሬ

**አዘጋጆች፡** ተስፋዬ ጋሻው፣ ሙሉነህ ገ/ሄደቶ እና ሮቢ ረዳ

**አምደኞች፡** መንሱር ደሴ እና መሀመድ አንዶሼ

**ግራፊክስና ሌይአውት፡** አርሴማ አንዳርጋቸው

## ዜናዎች

### ኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥን ለመግታት የዓለማቀፉን ጥረት እንደምትደግፍ በድጋሜ አረጋገጠች

የአየር ንብረት ለውጥ በዓለም ላይ እያደረሠ የሚገኘውን አሉታዊ ተፅኖ ለመግታትና ታሪካዊ የሆነውን የፓሪስ ስምምነት አምስተኛ ዓመት ለማሰብ እ.አ.አ. በዲሴምበር 12/2020 በተ.መ.ድ.፣ በእንግሊዝ እና ፈረንሳይ መንግስታት ትብብር ከፍተኛ ጉባኤ ተዘጋጅቷል። "የ2020 የአየር ንብረት ለውጥ ምኞት" በሚል መሪ ሀሳብ የተዘጋጀው ጉባኤ በበየነ መረብ የተካሄደ ሲሆን በስብሰባው ላይ ከ75 በላይ ሀገራትና መንግስታዊ ያልሆኑ መሪዎች የተካፈሉ ሲሆን ኢትዮጵያን በመወከል ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐብይ አህመድ ተሳትፈው መልዕክት አስተላልፈዋል።




ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ በጉባኤው ላይ ባደረጉት ንግግር እንዳሉት ኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖን ለመግታት "ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ልማት ስልትን በማቀድ እና ወደተግባር በመግባት የመሪነት ሚናን በግንባር ቀደምነት አሳይታለች"። ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ በንግግራቸው አክለው እንደገለፁት የአረንጓዴ ልማት ስልቱ ሀገሪቱ በቅርቡ ይፋ ባደረገችውና እ.አ.አ. ከ2021-2030 በሚተገበረው የአስር ዓመት የልማት ዕቅድ ሙሉ በሙሉ እንዲካተት ተደርጓል።

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ በንግግራቸው ጨምረው እንደገለፁት ኢትዮጵያ በሀገሪቱ የሚታየውን የአየር ንብረት ለውጥ አሉታዊ ተፅኖ ተጋላጭነትን ለመቀነስ ያለመ ብሄራዊ የማጣጣሚያ ዕቅድ አዘጋጅታ በማስጀመር በሁሉም የችግሩ ተጋላጭ ዘርፎች ተካቶ መተግበር ተጀምሯል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ በንግግራቸው አፅንኦት ሰጥተው እንደገለፁት ኢትዮጵያ የዓየር ንብረት ለውጥ ተፅኖን ለመግታት ያላትን ቁርጠኝነት በተግባር ለማረጋገጥ "አረንጓዴ አሻራ" የተሰኘና እ.አ.አ. ከ2019-2022 ባለው ጊዜ 20 ቢሊዮን ችግኞች የሚተከሉበት ብሄራዊ የአረንጓዴ ልማት መርሀ ግብርን አስጀምራ ባለፉት ሁለት አመታት ብቻ ዘጠኝ ቢሊዮን ችግኞችን መትከል ተችሏል።

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ በመልዕክታቸው መጨረሻ እንደገለፁት ምንም እንኳ የኮቪድ 19 ወረርሽኝ በርካታ ተግዳሮትን ቢደቅንም ኢትዮጵያ ሁለተኛውን በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ መቀነሻ ዕቅድ በማጠናቀቅ ላይ መሆኗን ገልፀው ለአለማቀፉ ማህበረሰብም የአየር ንብረት ለውጥን ተፅኖ ለመግታት በቁርጠኝነት እንዲረባረቡና ለታዳጊ ሀገራት የሚደረገውን የፋይናንስ ድጋፍ በማስፋት እንዲቀጥሉ ጥሪ አቅርበዋል። [ምንጭ]

## በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ ቅነሳን ለማሳካት የግብርና ዘርፉ ድርሻ

- **ብርሃኑ አሰፋ፣ በግብርና ሚኒስቴር የአካባቢና አየር ንብረት ለውጥ ማስተባበሪያ ዳይሬክተር**

የግብርና ሚኒስቴር የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የአፈፃፀም ሪፖርት እንደሚያሳየው እ.አ.አ. በ2020 የግብርናው ዘርፍ ለጥቅል ሀገራዊ የኢኮኖሚ እድገት (GDP) 34.6% ድርሻን ያበረከተ ሲሆን በተጨማሪም ዘርፉ 79% ያህሉን ሀገራዊ የስራ ዕድል የፈጠረና 79% ወደ ውጪ የሚላኩ ምርቶችንም ያስገኘ ነው። ይሁንና የግብርናው ዘርፍ በዝናብ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ግብርናው ለተለዋዋጭ የአየር ሁኔታዎችና የአየር ንብረት ለውጥ ማለትም የሙቀት መጨመር፣ ተደጋጋሚ ድርቅ እና ጎርፍ ለመሳሰሉት አደጋዎች ተጋላጭ ነው። የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በግብርና ላይ የተመሰረተ የአኗኗር ዘይቤን የሚከተሉ አካላት ለነዚህ አደጋዎች ተጋላጭነታቸው ከፍተኛ ነው። ከዚህም በተጨማሪ የአየር ንብረት ለውጥ በቀጣይነት ከእስካሁን የበለጠ አሉታዊ ተፅዕኖን እንደሚያሳድር ይገመታል። የግብርና እና የደን የአየር ንብረት ማጣጣምያ ስልት እንደሚያመላክተው የድርቅ በተደጋጋሚ መከሰት በዚሁ ከቀጠለ፣ እ.አ.አ. በ2050 አሁን ካለው ሀገራዊ የዕድገት ኢኮኖሚ ከ10% በላይ ቅነሳ ሊያስከትል ይችላል።

በዚህም ምክንያት፣ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የግብርና ስርዐት መዘርጋት እና የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ በመንግስት ቅድሚያ ከሚሰጣቸው የልማት አጀንዳዎች ዋነኞቹ ናቸው። ስለሆነም የብሄራዊ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ልማት (CRGE) ስልትን ለማስተግበር የግብርና እና የደን ልማት የአየር ንብረት ማጣጣምያ ስልት እ.አ.አ. በ2015 በማዘጋጀት የአየር ንብረት ለውጥ በዘርፉ ላይ የሚያስከትላቸውን ተፅኖዎች ለማጣጣምና ለመከላከል እየተሰራ ነው። ይህንን የዘርፉን ተጋላጭነት ለመቀነስ በግብርናው ዘርፍ የተለዩ መስኮች ላይ በልዩ ትኩረትና በርካታ ሀብት ተመድቦ በመሰራት ላይም ይገኛል። ይሁንና አሁንም ቢሆን የሀገራችንን ኢኮኖሚና ማህበረሰብ ተጋላጭነት ለመቀነስ ከእስካሁን በተሻለ እና ቀጣይነት ባለው ሁኔታ መስራት እና የሚያስፈልጉ ሀብቶችን ማሰባሰብም ያስፈልጋል። **ወደ ገፅ ፫**

ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

ቅፅ ፩፣ ቁጥር ፫

# ዜናዎች

## የአካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ተፈጥሮን መሠረት ያደረጉ የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያ መፍትሄዎች አስመልክቶ የክብ ጠረጴዛ ውይይት አስተናገደ

እ.አ.አ. በዲሴምበር 3፣ 2020 የአካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን በበይነ መረብ የታገዘ የክብ ጠረጴዛ ውይይት "የኢትዮጵያ ተፈጥሮን መሠረት ያደረጉ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖዎች የማጣጣሚያ መፍትሄዎች" በሚል ርዕሰ ጉዳይ አስተናግዷል። የክብ ጠረጴዛ ውይይቱን ከዓለም የማጣጣሚያ ኮሚሽን ጋር በጋራ የተዘጋጀ ሲሆን ዓላማውም በ2021 ለሚካሄደው ዓለማቀፍ የማጣጣሚያ ጉባኤ መነሻ ሆኖ እንዲያገለግል ታስቦ ነው። ሌላኛው የክብ ጠረጴዛው ውይይቱ ግብ የኢትዮጵያን ተፈጥሮን መሠረት ያደረገ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖዎች የማጣጣሚያ መፍትሄዎች ተጨባጭ እርምጃዎችና ተሞክሮዎች ለሌሎች በማሳያነት ለማቅረብ ነበር። በመሆኑም በመድረኩ የኢትዮጵያን ተፈጥሮን መሠረት ያደረገ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖዎች የማጣጣሚያ መፍትሄዎች ስኬቶች፣ ፈታኝ ሁኔታዎች፣ ትምህርት የተወሰደባቸው ጉዳዮች እና መልካም አጋጣሚዎች ለታዳሚዎቹ ቀርበዋል።

በውይይቱ ወቅት የኢትዮጵያን ተፈጥሮን መሠረት ያደረገ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖዎች የማጣጣሚያ መፍትሄዎች የተመለከቱ ጥናቶች ቀርበው ውይይት የተካሄደ ሲሆን ከቀረቡት የተግባር አፈፃፀም ውስጥም የተጎሳቆሉ የመሬት ገፅታዎች መልሰው እንዲያገግሙ የተሠሩ የችግኝ ተከላ፣ ዘላቂ የመሬት አያያዝና አጠቃቀም፣ የውሀና የደን ሀብት ጥበቃና የሀብት ማሰባሰብ ተግባራት ይገኙበታል።

የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ኮሚሽነር ክቡር ፕ/ር ፍቃዱ በየነ ሁነቱን በይፋ ሲከፍቱ ባሰተላለፉት መልዕክት አፅንኦት ሰጥተው እንደገለፁት ሀገራት ተፈጥሮን መሠረት ያደረጉ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖዎችን ለመቀነስ ተፈጥሯዊ መፍትሄዎችን ቅድሚያ ሰጥተው በመተግበር ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አቅም መገንባት ያስፈልጋቸዋል። ኮሚሽነሩ አክለውም ሀገራቸው ጉዳዩን አስመልክቶ ቁርጠኛ መሆኗን ገልፀው በቀጣይም የአየር ንብረትን ዘርፈ ብዙ ተፅዕኖዎችን ለመግታት ተፈጥሮን መሠረት ባደረጉ የአየር ንብረት ለውጥ አማራጮች ላይ ከሁሉም ባለድርሻዎች ጋር በትብብር እንደምትሰራ ገልፀዋል። ኮሚሽነሩ በመጨረሻም ሁሉም ያደጉ ሀገራትና የልማት ተቋማት ኢትዮጵያን ተፈጥሮን መሠረት ያደረጉ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖዎችን ለመቀነስ የሚረዱ ስልቶችን በመተግበር ላይ በቴክኒክና በፋይናንስ እንዲደግፉ ጥሪ አቅርበዋል።

## በኢትዮጵያ ዘላቂና ከአየር ንብረት ጋር ተስማሚ የሆኑ ማቀዝቀዣዎችን ጥቅም ላይ ማዋል ተስፋ እንዳለው ተገለፀ

በአለማችን በስፋት ለአየር እና ለምግብ ማቀዝቀዣነት የምንጠቀምባቸው መሳሪያዎች በዋነኛነት የሚጠቀሙት ሰው ሰራሽ የሆኑ የፍሎራየድ ጋዞችን

ወደ ገፅ ፬

ከገፅ ፪ የቀጠለ...

## ለአየር ንብረት ለውጥ አሉታዊ ተፅዕኖዎች ምላሽ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖዎችን ለመቋቋም እና ተጋላጭነትን ለመቀነስ የተለዩ አማራጮች

የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ቅነሳን በተመለከተ የግብርናው ዘርፍ በሁለት ንዑሳን ዘርፎች ተለይቶ የሚተገበር ነው። እነዚህም የአፈር እና የእንስሳት ሀብት ልማት ዘርፎች ናቸው። ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ልማት ስልት ዝርዝር ትንታኔ እንደሚያመላክተው የግብረናው ዘርፍ አሰራር በነበረበት ከቀጠለ፣ እ.አ.አ. በ2010 ይለቀው የነበረው 75 ሚ.ሜ.ቶን የካርቦን ዳዮክሳይድ እኩሌታ ($MtCO_2e$) የሙቀት አማቂ ጋዞች ድርሻ በ2030 ወደ 185 ሚ.ሜ.ቶን የካርቦን ዳዮክሳይድ እኩሌታ ይጨምራል። ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ልማት ስልት እና ሀገራዊ በፈቃደኛነት ላይ የተመሰረተ የአየር ንብረት ተፅዕኖ መቀነሻ ዕቅድ (NDC) በግብርና ዘርፍ በሚገኙ የአፈርና የእንስሳት ልማት ንዑሳን ዘርፎች እንዲተገበሩ የሚከተሉት 7 ዋና ዋና ስልታዊ እርምጃዎችን ለይተዋል።

### ከአፈር ጋር ተያይዞ የተለዩ እርምጃዎች (initiatives)

- የተሻሻሉ ግብዐቶችን በመጠቀምና የተሻሻለ የተረፈ ምርት አስተዳደር ስርዓትን በመዘርጋት የግብርና ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፤
- በቆላማ ስፍራዎች አዳዲስ የእርሻ መሬቶችን በመስኖ በማልማት ለግብርና የሚውሉ መሬቶች መስፋፋትን መግታት፤
- ዝቅተኛ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ያላቸው የግብርና ቴክኖሎጂዎችን ተግባራዊ ማድረግ።

### ከእንስሳት ሀብት ልማት ጋር ተያይዞ የተለዩ እርምጃዎች (initiatives)

- የእንስሳት ሀብት የምርት ሰንሰለት ስርዓትን በማሻሻል ምርታማነትን ማሳደግ፤
- ዝቅተኛ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ያላቸውን የእንስሳት ተዋጽዎችን ለፕሮቲን ምንጭነት መጠቀምን ማበረታታት፤
- የግብርና ስርዓቱን መመክነክ (mechanize) እና፣
- የሰፋፊ የግጦሽ መሬቶችን የካርበን ይዘት በማጎልበት የመሬቱን ምርታማነት ሊያሻሽል የሚያስችል የመሬት አስተዳደር ስርዓትን መተግበር።

ወደ ገፅ ፬

## ዜናዎች

**ከገፅ ፫ የቀጠለ...**

(ኤፍ-ጋዝ) ነው። ምንም እንኳን እነዚህ ጋሶች የተፈጠሩት ሌሎች በኦዞን ሽፋን ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ጋዞችን ለመተካት ቢሆንም ከ 'ካርቦን ዳይኦክሳይድ' ጋር ሲነፃፀሩ ለዓለም ሙቀት መጨመር የሚያበረክቱት ድርሻ በ10,000 እጥፍ ነው። በተጨማሪም ከማቀዝቀዣ ዘርፍ የሚወጣው የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት እ.አ.አ. በ2030 የሚኖረው ድርሻ 13% እንደሚሆን ሲገመት፣ ይህም አሁን በየብስ ትራንስፖርት ከሚለቀቀው የበካይ ጋዞች ልቀት ተመሳሳይ ድርሻ ያለው ነው።

በኢትዮጵያ የቤትም ሆነ የንግድ ቦታዎች የማቀዝቀዣ መሰሪያዎች ተደራሽነት ውስን ነው። የግብርና ውጤቶችን እድሜ ለማራዘም ማቀዝቀዣዎች በጣም አስፈላጊ ሲሆኑ፣ የግብርናው ዘርፍ ደግሞ ለኢትዮጵያ የኢኮኖሚ እድገት ወሳኝ ነው። በቅርብ ግዜ እየወጡ ያሉ ዘላቂ የማቀዝቀዣ መሳሪያ ግኝቶች ኢትዮጵያ በቀጥታ ወደ ቀልጣፋ እና ለአየር ንብረት ተስማሚ ወደሆኑ የማቀዝቀዣ ውጤቶች እንድታመራ ያስችሏታል። እነዚህ ማቀዝቀዣዎች ለህክምና አገልግሎትም አስፈላጊ ሲሆኑ ይህም ቅዝቃዜ የሚያስፈልጋቸው ክትባቶችን፣ የኮቪድ 19ን ጨምሮ ለማጓጓዝነት ያገለግላሉ።

የተ.መ.ድ. ዋና ፀሀፊና የተባበሩት መንግስታት የአየር ንብረት ለውጥ ስምምነት አባል ሀገራት የወቀቱ ሊቀመንበር የሆነችው ሀገረ እንግሊዝ እ.አ.አ. በ12 ዲሴምበር 2020 በጋራ በመሆን ከሚያዘጋጁት የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ ቀደም ብሎ የአባል ሃገራቱ 26ኛ ጉባኤ መሪ ቡድን በእንግሊዝ መንግስት አስተናጋጅነት እ.አ.አ. በ10 ዲሴምበር "ሀይልን በጤታማነት የሚጠቀሙ ምርቶች ለሀገራት በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ዕቅድ እና የተጣራ የዜሮ ልቀት ስኬት" በሚል ርዕስ ጉዳይ ውይይት አዘጋጅተዋል። ጉባኤው ከፍተኛ ባለስልጣናት ባሉበት አገሮች የሙቀት ማቀዝቀዣ ምርቶችን ጨምሮ በአጠቃላይ የሀይል ቆጣቢ መገልገያ ቁሳቁሶችን የአቅርቦትና የአጠቃቀም ጥረቶችን እንዲያጋሩ መድረክ ፈጥሯል።

በዚህ ጉባኤ ላይ በአቅራቢነት ከተካፈሉ ሀላፊዎች መካከል አንዱ የኢትዮጵያ የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ኮሚሽነር ክቡር ፕ/ር ፍቃዱ በየነ ነበሩ። በጉባኤው ከተከናወኑ ጉዳዮች አንዱ "የኪጋሊ የማቀዝቀዣዎችን ውጤታማነት ማሳደጊያ" የተሰኝ ፕሮግራም ድጋፉ እንዲደረግላቸው የተለዩ ሀገራትን ይፋ አድርጓል። ድጋፉ የተደረገው መካከለኛና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ሀገራት በቀጣዩ ከ2 እስከ 3 ዓመታት በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖን ለመቀነስ ውጤታማ የሆኑ የሙቀት ማቀዝቀዣዎች ተጠቃሚነትን እንዲያሳድጉ ለመደገፍ ነው። ከተዋወቁት ፕሮጀክቶች አንዱ ከኢትዮጵያ ሲሆን የፕሮጀክቱ አላማም የግበርና ውጤቶችን የሙቀት ማቀዝቀዣዎች የተጠቃሚነት ሰንሰለትን ለማሻሻል ነው። ፕሮጀክቱ በቀጣይ 2.5 ዓመታት ለአካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን እና ለኢትዮጵያ 'ኢነርጂ' ባለስልጣን የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል።

**ከገፅ ፫ የቀጠለ...**

**እስካሁን የተደረጉ ጥረቶችና የተገኙ ውጤቶች**

ወቅታዊና የረጅም ግዜ ተለዋዋጭ የአየር ሁኔታዎች የሚያስከትሉትን አደጋዎች ለመቋቋም ከላይ የተጠቀሱት እርምጃዎች ላይ በመመርኮዝ የዘርፉ የአየር ንብረት ለውጥ መቋቋሚያ ስትራቴጂ 41 ዝቅተኛ የካርበን ለቃቂ የልማት የትኩረት መስኮችን ለይቶና ቅድሚያ ሰጥቶ በመተግበር ላይ ይገኛል።

በእነዚህ የትኩረት መስኮች የሚሰራው የስራ ድምር ውጤትም ዘርፉ የልማት ግቦቹን እያሳካ እግረ መንገዱን ደግሞ እ.አ.አ. በ2030 90 ሚ.ሜ.ቶን የካርቦን ዳዮክሳይድ እኩሌታ የሙቀት አማቂ ጋዝ ወደ ከባቢ አየር እንዳይለቀቅ ይቀንሳል።

በአፈርና እንስሳት ሀብት ልማት ንዑሳን ዘርፎች የተለዩና ዒላማ የተቀመጠላቸውን የትኩረት መስኮች ለማሳካት ባለፉት አምስት አመታት ልዩ ትኩረት የተሰጣቸውና ከፍተኛ የህዝባዊ መዋዕለ ንዋይ የፈሰሰባቸው ስራዎች ተሰርተዋል። እነዚህም በተቀያያሪ የአየር ንብረት ለውጥ ውስጥ ለሚደረገው መረባረብ የግብርናው ዘርፍ ድርሻን አሳድገዋል። ከተሰሩት ስራዎች መካከልም:-

- 1.2 ሚሊዮን ኩንታል የተሻሻለ ዘር እና 1.6 ሚሊዮን ቶን ማዳበሪያ በመጠቀም የዋና ዋና ሰብል ምርቶችን ምርታማነት ለማሳደግ በተሠራው ስራ እ.አ.አ. በ2013/14 ከነበረው የ270 ሚሊዮን ኩንታል ምርት እ.አ.አ. በ2019/20 ወደ 335 ሚሊዮን ኩንታል ማሳደግ ተችሏል።
- እ.አ.አ. በ2019/2020 በእንስሳት ሀብት ልማት ንዑስ ዘርፍ በተሠራ ስራ በ2013/2014 ከተገኘው ውጤት ጋር ሲነፃፀር የወተት፣ የስጋ፣ የእንቁላልና የመኖ ምርቶች እንደየቅደም ተከተላቸው በ3%፣ 9%፣ 63% እና በ14% እድገት አሳይተዋል። ከንዑስ ዘርፉ ይለቀቅ ከነበረው 12.06 ሚ.ሜ.ቶን የካርቦን ዳዮክሳይድ እኩሌታ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀትም ተቀንሷል።
- በጥቅሉ ሲታይ በግብርና ዘርፍ በተሠሩ ስራዎች በሁለተኛው ሀገራዊ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን (2015-2020) 36.84 ሚ.ሜ.ቶን የካርቦን ዳዮክሳይድ እኩሌታ እኩሌታ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀትን መቀነስ ተችሏል።

**ወደ ገፅ ፭**

ከገፅ ፬ የቀጠለ...

## የግብርና ዘርፍ የቀጣይ 10 ዓመታት የልማት ዕቅድ

የዓየር ንብረት ለውጥ በሰው ልጆች ላይ በደቀነው ንፍቀ ክበባዊ እውነታ ውስጥ ባለንበት በዚህ ወቅት ተፈጥሮ በለገሰችን ታላላቅ ሀብቶች ላይ ማለትም በውሀ፣ በመሬት፣ በአፈርና በሌሎች ስርዐተ ምህዳሮች አስተዳደር ላይ ጥበቃ ማድረግ ያስፈልጋል። ከዚህ አኳያም የግብርና ዘርፍ የቀጣይ አስር አመታት የልማት ዕቅድ ለዓየር ንብረት ለውጥ ለማይበገር የዐዝዕርት ልማት፣ ለእንስሳት ሀብት ልማት፣ ለተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና ለስነ ምህዳሮች አገልግሎት ጉልህ ትኩረት ሰጥቷል።

የግብርናው ዘርፍ የቀጣይ አስር ዓመታት የልማት ዕቅድ የተቀረፀው በሀገር ደረጃ ተግባራዊ እየተደረጉ የሚገኙት ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ልማት ስልት፤ የብሄራዊ በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ አሉታዊ ተፅዕኖዎች መቀነሻ ዕቅድ እንዲሁም የግብርና እና የደን ልማት የአየር ንብረት ማጣጣምያ ስልት ቅድሚያ ተሰጥቷቸው እንዲተገበሩ የለዩዋቸውን ጉዳዮች በቀጥታ በመውሰድና እያንዳንዱን ስትራተጂካዊ ጉዳይ ተተግብሮ እ.አ.አ. በ2030 ሊደረስባቸው ወደሚያስችል ዒላማነት በመቀየር ነው። በቀጣዩ ሰንጠረዥ 1 እንደተመላከተው በእያንዳንዱ ግቦች የሚቀነሰው የሙቀት አማቂ ጋዞች መጠንም ተለይቶ ታቅዷል።

**ሰንጠረዥ 1. የግብርና ዘርፍ አመታዊ፣ የ5 ዓመታትና የ10 ዓመታት የሙቀት አማቂ ጋዞች ቅነሳ ዒላማዎች በሚ.ሜ.ቶን የካርቦን ዳዮክሳይድ እኩሌታ**

| ዘርፍ | 2019/20 | 2020/21 | 2021/22 | 2022/23 | 2023/24 | 2024/25 | 5 ዓመታት | 2025/26 | 2026/27 | 2027/28 | 2028/29 | 2029/30 | 10 ዓመታት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሰብል | 7.23 | 3.67 | 3.67 | 3.67 | 3.67 | 3.67 | 18.35 | 2.45 | 2.45 | 2.45 | 2.45 | 2.45 | 30.60 |
| የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ | 17.55 | 2.70 | 2.70 | 2.70 | 2.70 | 2.70 | 13.5 | 1.80 | 1.80 | 1.80 | 1.80 | 1.80 | 22.5 |
| የእንስሳት ሀብት | 12.06 | 4.313 | 4.313 | 4.313 | 4.313 | 4.313 | 21.565 | 2.875 | 2.875 | 2.875 | 2.875 | 2.875 | 35.94 |
| አጠቃላይ | 36.84 | 10.683 | 10.683 | 10.683 | 10.683 | 10.683 | 53.415 | 7.125 | 7.125 | 7.125 | 7.125 | 7.125 | 89.04 |

## የግብርና ዘርፍ የቀጣይ 10 ዓመታት የልማት ዕቅድ ሲተገበር ሊጤኑ የሚገባቸው ቁልፍ ነጥቦች

- በሀገራዊ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ስልት እና በብሄራዊ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖ መቀነሻ እቅድ ላይ ተለይተው የተቀመጡት እቅዶች በዘርፉ የመደበኛ ስራዎች የልማት ዕቅድ፣ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ውስጥ ተካተው በሁሉም መዋቅሮች ደረጃ መተግበራቸው ለሀገራዊ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖ መቀነሻ እቅድ ስኬት ወሳኝ መሆኑን መገንዘብ፣
- የአየር ንብረት ለውጥን አሉታዊ ተፅዕኖዎች መግታትና አይበገሬነትን መገንባት በተለያዩ ደረጃዎች የሚገኙ የሁሉም ባለድርሻዎችን ቅንጅታዊ ሀላፊነት የሚሻ መሆኑን መረዳት፣
- የልማት ዕቅዱን የሚተገብሩ የዘርፍ ፈፃሚ መስሪያ ቤቶች ስራውን በባለቤትነት ወስደው መተግበር፤ ከዓለማቀፍ ጥረቶች ጋር በትብብር መስራትና ስኬትን ማረጋገጥ እንዲሁም በየደረጃው የሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች በሂደቱ መሳተፋቸውን ማረጋገጥ፣
- የግሉ ዘርፍ የማህበረሰቡን የአየር ንብረት ለውጥ ተጋላጭነት ሊቀንሱ በሚችሉ ዘርፎች የሚያከናውኑት ኢንቨስትመንት ጠቃሚ ሚናን ይጫወታሉ። በተመሳሳይ የልማት አጋር አካላት የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖን ለመቀነስ በሚደረገው ጥረት በቴክኒክ ድጋፍ፣ በአቅም ግንባታ እና በፕሮጀክት ትግበራ ጉልህ ድጋፍ ማበርከት ይችላሉ፣
- በግብርናው ዘርፍ እንዲተገበሩ የተለዩትን 41 የዘርፉ የልማት አማራጮችን/ግቦችን ለማስተግበር ለግብርና ሚኒስቴር ከሚመደበው በጀት በተጨማሪ ዛሬ ላይ 200 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ሲያስፈልግ እ.አ.አ. በ2030 ደግሞ 600 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ተጨማሪ ኢንቬስትመንት ያስፈልጋል። ይህንን አስፈላጊ የገቢ ምንጭ ለማሰባሰብ በጥምረት መስራትን ይጠይቃል።

## ሁነቶች

ዓለማቀፉን የኮሮና ወረርሽኝ መከሰት ተከትሎ በርካታ አካባቢ ነክና ዘላቂ ልማትን ማረጋገጥ አልመው የታቀዱ ሁነቶች ተራዝመዋል ወይም ተሰርዘዋልም። ይሁንና ክፍተቱን ለመሙላት የተለያዩ ምክክሮችና ትብብሮች የቀጠሉ ሲሆን ከነዚህም መካከል የሚከተሉት ሁነቶች በበይነ መረብ አማካይነት ይከናወናሉ። እነዚህ ሁነቶች ለተሳታፊዎች ክፍት የሆኑ ሲሆን እያንዳንዱን ሁነቶች በተመለከተ ዝርዝር መረጃ ለማግኘት ካስፈለገዎ የማስፈንጠሪያ ቁልፉን በመጫን ማግኘት ይችላሉ።

- አዳዲስ የሀገራት የአየር ንብረት ለውጥ ውጥኖችን ለመዳሰስ የሚረዱ የመረጃ መተግበሪያዎች፤ ደብልዩ. አር. አይ.፣ እ.አ.አ. ዲሴምበር 2020 I **ምንጭ**
- የመንግስት በጀት እና 'አረንጓዴ ማገገም' ፤ ደብልዩ. አር. አይ.፣ እ.አ.አ. ዲሴምበር 2020 I **ምንጭ**
- የተለያዩ የሀይል አማራጮችን ለመጠቀም የተደረገ ዝግጅት መሪ ንድፎችና ዕቅዶች፣ የአየር ንብረት መስተጋብሮች፣ ክላይሜት ሊንክስ፣ እ.ኤ.አ. ዲሴምበር 2020 I **ምንጭ**
- የሁለት ዲግሪ እርምጃ ለምግብና ግብርና፣ ሲ.ሲ.ኤ.ኤፍ.ኤስ.፣ እ.ኤ.አ. ዲሴምበር 2020 I **ምንጭ**
- ከአምስት አመት በኋላ፤ የፓሪሱን ስምምነት ማክበር እና የወደፊቱን መንገድ መቀየስ፤ ደብልዩ. አር. አይ.፣ እ.አ.አ. ዲሴምበር 2020 I **ምንጭ**
- የኢንተርኔት ስልጠና-የግሉ ዘርፍና የመንግስት ትብብር - የመስኖ ልማት ውጤታማነት ማሻሻያ ስልቶች (በግል ጊዜና ፍጥነት የሚወሰን)፣ እ.ኤ.አ. ዲሴምበር 2020 | **ምንጭ**
- የኢንተርኔት ስልጠና፤ ዝቅተኛ የካርቦን ልቀት ላይ የተመሰረተ ልማትን እውን ለማድረግ የሚረዱ የፖሊሲ ማዕቀፎች፤ ከንድፍ እስከ ትግበራ (በግል ጊዜና ፍጥነት የሚወሰን)፣ እ.ኤ.አ. ዲሴምበር 2020 | **ምንጭ**
- የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያ ጉባኤ እ.ኤ.አ. ጃንዋሪ 2021 I **ምንጭ**
- የመጪው ዘመን የማዕከላዊ ባንክ አሰራር: የአየር ንብረት ለውጥ፣ ኢፍትሀዊነት፣ የፋይናንስ አለመረጋጋት፣ ሃይንሪክ ቦል ፋውንዴሽን፣ እ.አ.አ. ፌብሯሪ 2020 I **ምንጭ**

## የኢትዮጵያ የከተሞች ደረቅ ቆሻሻ ዘርፍ ለብሄራዊ በፈቃደኛነት ላይ ለተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ ቅነሳ የሚያበረክተው ሚና

❑ **ግርማ ገመቹ፤ በአካባቢ፣ ደን እና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን የደረቅና አደገኛ ቆሻሻዎች ህግ ተከባሪነት ክትትል ዳይሬክተር**

የኢትዮጵያ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የአየር ንብረት ለውጥ ዕቅድ (NDC) እንደሚያመላክተው እ.አ.አ በ 2030 በተለመደው አሰራር ቢኬድ ሊደርስ ከሚችለው ጋር ሲነፃፀር የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀትን በ64% የመቀነስ አላማ አስቀምጧል። በኢትዮጵያ ከዚህ በተጨማሪ የማህበረሰቡን፣ የአካባቢውንና የኢኮኖሚውን ለአየር ንብረት ለውጥ ተጋላጭነት ለመቀነስ እ.አ.አ በ2011 እና 2017 ይፋ በሆኑት ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ (CRGE) ስትራቴጂና ሀገራዊ የማጣጣሚያ ዕቅድ (NAP) ላይ በመመርኮዝ የማጣጣሚያ ተግባራት ተለይተዋል። ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂው አንዱ ምሰሶ በትራንስፖርት፣ በኢንዱስትሪ እና በሕንፃዎች ላይ ኃይል ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎችን በማስፋፋት የኃይል ብክነትን ማስቀረት ነው።

ከተሞች ለሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት ያላቸው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው። 80% የሚሆነው የአለም ጥቅል የኢኮኖሚ እድገት (GDP) እ.አ.አ በ2018 የተገኘው ከከተሞች ሲሆን በተጨማሪም ከተሞች በአለም ከሚመረተው የሀይል መጠን 80% የሚሆነውን ይጠቀማሉ። ስለዚህ የከተማ እቅድና አስተዳደር እንዲሁም ዘላቂ የትራንስፖርት ዘዴ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀትን ለመቀነስ ወሳኝ ናቸው። ልቀትን የሚጨምረው የከተሞች መስፋፋት ብቻ ሳይሆን ልቅ የሆነ የከተሞች እድገትና እንቅስቃሴ እንዲሁምየህብረተሰቡ የሃይል አጠቃቀምና የቆሻሻ አያያዝ ሲሆን እነዚህም ከተሞች ለብክለትና ለአየር ንብረት ለውጥ የሚኖራቸውን ሚና ይወስናሉ።

በኢትየጵያ የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት እና የከተሞች ደረቅ ቆሻሻ ከፍተኛ ትስስር አላቸው። ፈጣን የከተሞች መስፋፋት ከህዝብ ብዛት ዕድገት ጋር ሲጣመር የደረቅ ቆሻሻ በ24% በአመት እንዲጨምር አድርገታል። በተጨማሪ ከሚወጣው ቆሻሻ ውስጥ በአማካይ 50% ብቻ በአግባቡ የሚሰበሰብ ሲሆን ከተሰበሰበውም ውስጥ 95% የሚሆነው ከቁጥጥር ውጪ በሆኑ መጣያ ቦታዎች ላይ ይቀበራል። ቀሪው 50% ያለምንም ቁጥጥር የሚጣል ሲሆን አብዛኛውም ክፍት በሆነ ቦታ ይቃጠላል።

በአጠቃላይ ኢትዮጵያ ያላት 150 ሚ.ሜ.ቶን የካርቦን ዳዮክሳይድ እኩሌታ (MtCO2e) የሚሆነው የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት ከአለም ጋር ሲነፃፀር 0.3% ብቻ ይይዛል።

**ወደ ገፅ ፯**

ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ
ቅፅ ፩፣ ቁጥር ፫

## ልዩ ልዩ ህትመቶች

### ውጤታማ የሆኑ ማቀዝቀዣ ቁሶች ጠቀሜታ




"ዘ ኢኮኖሚስት ኢንተለጀንስ ዩኒት" ባወጣው አዲስ የመረጃ ምንጭ የተሻለና ውጤታማ የሆኑ የሙቀት ማቀዝቀዣ ምርት ውጤቶችን ተግባራዊ ማድረግ $3.5 ትሪሊዮን ያህል ሀብትን በቀጣይ አስር አመታት እንደሚቆጥብ ገልጿል። በዚህም የተነሳ 7.6 ጊጋ ቶን ያህል የተቃጠለ በካይ ጋዝ ($Co_2$) እንደሚቀንስ ተገልፃል። **ምንጭ**

### የተ.መ.ድ.የአየር ንብረት ለውጥ ማዕቀፋዊ ስምምነት የፆታ እኩልነት የኪስ ማስታወሻ




ኢ.ሲ.ቢ.አይ የተሰኘውና ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር በተገናኙ ጉዳዮች ላይ የአቅም ግንባታ ስራን የሚሰራው አካል በቅርቡ የተ.መ.ድ. የአየር ንብረት ለውጥ ማዕቀፋዊ ስምምነትን የተከለሰ የፆታ እኩልነት የኪስ ማስታወሻ መመሪያ ይፋ አድርጓል። የኪስ ማስታወሻ መመሪያው እ.አ.አ የ2019 የተሻሻለውን የሊማ የስርዐተ ፆታ ፕሮግራም እና ዕቅድን እንዲሁም ስርዐተ ፆታን በአየር ንብረት ለውጥ ዕቅድና ትግበራ ለማካተት የተዘጋጁ ሰነዶችን ያካተተ ነው። **ምንጭ**

### እ.አ.አ. የ2020 የዓለም አቀፍ ደን ነባራዊ ሁኔታ




የዓለማቀፍ የደን ነባራዊ ሁኔታ ዘገባ የአለማችን ደኖች ያሉበትን ሁኔታ፣ በቅርብ የወጡ ወሳኝ ፖሊሲና ተቋማዊ ለውጦችን እንዲሁም የደን ዘርፉን የተመለከቱ ቁልፍ ጉዳዮችን ይዞ ወጥቷል። **ምንጭ**

**ከገፅ ፮ የቀጠለ...**

150 ሚ.ሜ.ቶን የካርቦን ዳዮክሳይድ እኩሌታ ከሚሆነው እ.አ.አ በ2010 ከተለቀቀው የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት ውስጥ 37% የሚሆነው ከግብርናው ዘርፍ ሲሆን 50% ደግሞ ከደኑ ዘርፍ ነው። የሀይል፣ የትራንስፖርት፣ የኢንዱስትሪና የከተማው ዘርፎች እያንዳንዳቸው 3% አስተዋፅኦ በመያዝ ይከተላሉ።

እ.አ.አ በ2010 የሕንፃዎች ልቀት 5 ሚ.ሜ.ቶን የካርቦን ዳዮክሳይድ እኩሌታ የነበረ ሲሆን የልቀቱ ምንጮችም ደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻ (3 ሚ.ሜ.ቶን የካርቦን ዳዮክሳይድ እኩሌታ) እና ከአገር አቀፉ የኤሌክትሪክ ኃይል መረብ ውጪ በግል የሚመረት የኤሌክትሪክ ኃይል (2 ሚ.ሜ.ቶን የካርቦን ዳዮክሳይድ እኩሌታ) ናቸው።

የከተሞች የህዝብ ብዛት ማደግ የቆሻሻን ብዛት እንዲሁም በግል የሚንቀሳቀሱን የሃይል ምንጮች ፍላጎትን እንደሚጨምር ይገመታል። በመሆኑም ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂው የዘርፉ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት እ.አ.አ በ2010 ከነበረበት የ5 ሚ.ሜ.ቶን የካርቦን ዳዮክሳይድ እኩሌታ እ.አ.አ በ2030 ወደ 10 ሚ.ሜ.ቶን የካርቦን ዳዮክሳይድ እኩሌታ እንደሚጨምር ያሳያል። ይህ ጭማሪም 25% ከመረብ ውጪ በናፍጣ ከሚመረት የኤሌክትሪክ ኃይል ሲሆን 75% ደግሞ ከቆሻሻ ይሆናል።

ባጠቃላይ የከተሞችን ለሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀትን ያላቸውን አስተዋጸኦ፣ በዋነኛነት ደግሞ ከደረቅ ቆሻሻ የሚወጣውን የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀትን ከግምት ውስጥ በማስገባት የኢትዮጵያ መንግስት በአለም አቀፉ የአካባቢ ፋሲሊቲ (GEF) ድጋፍ እ.አ.አ ከ2015 ጀምሮ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን ሲተገብር ቆይቷል። በ6 ከተሞች የደረቅ ቆሻሻን የማምረት እና ቀድሮ መጠቀም ፕሮጀክት እንዲሁም ሌሎች ከተማን መሰረት ያደረጉ የቆሻሻ አያያዝ ፕሮጀክቶች ለቆሻሻ አያያዝ መሰረተ ልማት መስፋፋት እና ለማህበረሰብ ተሳትፎ መጨመር ከፍተኛ አስተዋፅኦ ከሚያደርጉት ውስጥ ተጠቃሽ ናቸው።

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚ/ር ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚንና በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የአየር ንብረት ለውጥ ዕቅድ ትግበራን ለማገዝ የአካባቢ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ተከታታይ የሆነ የከተማ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ትግበራ ክትትል በ721 ነባርና አዳዲስ ከተሞች ላይ አካሂዷል። ይህ ፅሁፍ በዚህ ዳሰሳ የተለዩ ተግዳሮቶችና ምክረ ሀሳቦችን ያቀርባል።

**ወደ ገፅ ፰**

**ከገፅ ፯ የቀጠለ...**

### ከቆሻሻ የሚወጣውን ልቀት ለመቀነስ በኢትዮጵያ ያሉት ደንቦችና ቁርጠኝነት

ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂ ይፋ ከሆነበት እ.ኢ.አ ከ2011 ዓ.ም አንስቶ ኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥ ጠንካራ የማስተሰረያና የማጣጣሚያ የህግና ተቋማዊ ማዕቀፍ ዘርግታለች። በሁለቱ ተከታታይ ሀገራዊ ዕቅዶች ማለትም እ.ኢ.አ ከ2010 እስከ 2020 የተተገበሩት የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ 1 እና 2 አስፈላጊ ለሆኑ ኢንዱስትሪዎችና ዘርፎች የተለያዩ ዒላማዎችና ስትራቴጂዎች ሲያወጡ እና ሲያጠናክሩ ቆይተዋል። እነዚህ ዕቅዶች ኢትዮጵያ ለአየር ንብረት ለውጥ ትግበራ የሰጠችውን ትኩረት ያሳያሉ። እንደምሳሌነት በየከተማው ዘርፍ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ 2 ላይ 70% ከቤት የሚወጣ ደረቅ ቆሻሻን መሰብሰብ እና ከዚህም ውስጥ 30% የሚሆነውን በተለያየ መንገድ ለሀይል ምንጭ መጠቀምን ጨምሮ እንደገና ጥቅም ላይ ማዋል የሚል ኢላማ ተቀምጧል። ከዚህ በተጨማሪ እ.ኢ.አ የ2014ቱ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ስትራቴጂ በተሻሻለ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀትን ለመቀነስ ሁነኛ መሳሪያ ሁኖ ቀይቷል።

በአለም ደረጃ የአየር ንብረት ለውጥን ለመቀነስ በሚደረጉ ቁርጠኝነት ረገድ እ.ኢ.አ በ2017 ዓ.ም እና 2019 ዓ.ም የኢትዮጵያ መንግስት የፓሪስ ስምምነት እና የኪጋሊ ማሻሻያን በቅደም ተከተል አፅድቋል።

### የኢትዮጵያ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የአየር ንብረት ለውጥ ዕቅድን (NDC) በከተማው ዘርፍ ለማሳካት የገጠሙ ተግዳሮቶች

ባለፉት አምስት አመታት አብዛኞቹ የክልል መንግስታት የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ በጀታቸውን የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀትን ለመቀነስና ጥንቃቄ የተሞላበት የቆሻሻ አወጋገድና አሰባሰብን ለመተግበር ከ10-15% በአመት አሳድገዋል።

ሆኖም ኢትዮጵያ በከተማው ዘርፍ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ረገድ ያስቀመጠቻቸውን ዒላማዎች ለማሳካት በርካታ ተግዳሮቶች ገጥሟታል። የማስተሰረያ ዘዴዎች ትግበራ ለመሰረተ ልማት ዝርጋታ፣ ለቴክኖሎጂና ለህብረተሰብ ግንዛቤ የሚውል በርካታ መዋዕለ ንዋይ ይፈልጋል። የማስተሰረያ ዘዴዎችን በመተግበር የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀትን ለመቀነስ የሚያስፈልገው በጀት ከ187 ከተሞች በተገኘው ግምት መሰረት 2.7 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ይገመታል። የተሻሻለና የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ የገጠሙት ተግዳሮቶች የሚከተሉትን ያጠቃልላል፤

- **ቆሻሻን ከምንጩ መለየት:-** በግንዛቤ እጥረት፣ የፖሊሲ መመሪያ አለመኖርና በመሰረተ ልማት እጥረት ምክንያት ቆሻሻን ከምንጩ መለየት ላይ ከፍተኛ ክፍተት አለ። በዚህም ምክንያት አብዛኞቹ ቆሻሻ መሰብሰቢያና ማጓጓዣ መሰሪያዎች የተደባለቀ ቆሻሻን ይይዛሉ።

- **መሰብሰብና ማጓጓዝ:-** በአማካይ ቆሻሻን የመሰብሰብ ሂደት 50% ይተመናል ይህንን እ.ኢ.አ በ2030 እንደታቀደው ወደ 100% ለማሳደግ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ ያስፈልጋል። ቆሻሻን ለመሰብሰብና ለማጓጓዝ የሚሰበሰበው ክፍያ የስራ ማስኬጃ ወጪን ብቻ የሚሸፍን ሲሆን አገልግሎት መስጫ ቁሳቁሶችን ለማዘመን በቂ አይደለም።

- **የቆሻሻ አያያዝ:-** በኢትዮጵያ የሚሰበሰበው ቆሻሻ 70% የሚሆነው የሚበሰብስ (organic) ነው። የተቀናጀ የቆሻሻ አያያዝን ማለትም ምንጩቹን መቀነስ፣ መለየት፣ በድጋሚ ጥቅም ላይ ማዋልና አበስብሶ ለማዳበሪያነት መጠቀምን አለመተግበር በቆሻሻ መጣያ በታዎች ላይ ከፍተኛ ጫና ሲፈጥር በርካታ የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀትንም እየጨመረ ይገኛል።

- **ተቋማዊ ተግዳሮቶች:-** ምንም እንኳን በርካታ ፖሊሲና ደንቦች በደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ ላይ ቢኖሩም ኢትዮጵያ ይህንን ማስፈፀሚያ የህግ ስርዐት የላትም። ከዚህ በተጨማሪ በሀገራዊ፣ በክልል እና በከተማ አስተዳደሮች መካከል የተደራረበ ሀላፊነት መኖር የቅንጅት ክፍተት እንዲኖር አድርጓል።

### ምክረ ሀሳቦች

ከተሞች ለአለም የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት 70% ያህል ድርሻ አላቸው፤ ስለዚህ የኢትዮጵያ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የአየር ንብረት ለውጥ ዕቅድን ማሳካት የሚቻለው የከተሞች እቅድ አወጣጥን እና አስተዳደርን መቀየር እና ማሻሻል ሲቻል ብቻ ነው። በክልሎችና በከተሞች ተሞክሮንና ዕውቀትን በመለዋወጥ ግልፅና ውጤታማ ቅንጅታዊ አሰራርን በዘርፎች መካከል ማረጋገጥ ለኢትዮጵያ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የአየር ንብረት ለውጥ ዕቅድ መሳካት የግድ መሟላት ያለበት ቅድመ ሁኔታ ነው።

**ወደ ገፅ ፱**

**ከገፅ ፰ የቀጠለ...**

በመጨረሻም የኢትዮጵያን በፈቃደኛነት ላይ የተመሰረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖ መቀነሻ ዕቅድ ለማሳካትም ሆነ ወደ አረንጓዴ ኢኮኖሚ ለመሸጋገር ከተሞች እያጋጠማቸው ካለው ተግዳሮት ጋር የሚመጣጠን ሀብት ያስፈልጋል። ይህ ሀብትም ከመንግስት ወይም ከግሉ ዘርፍ ሊመነጭ ይችላል። የሚከተሉት ምክረ ሀሳቦችም በሀገር ውስጥ በዘርፉ ለሚንቀሳቀሱ ተዋንያን ቁልፍ ተግባራት ናቸው።

- **የፌደራል መንግስት የሀገሪቱ በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ መቀነሻ ዕቅድ በክልሎችና በከተሞች ዕቅዶች ውስጥ እንዲካተቱና እንዲተገበሩ በቂ የቴክኒክ ድጋፍ ማድረግና የመረጃና ፍሰቱ ከታችኛው የአስተዳደር እርከን እስከ ፌደራል ድረስ እንዲሳለጥ በቂ ድጋፍ ማድረግ ይኖርበታል።** የዚህ ድጋፍ መኖር ክልሎችና ከተሞች የሙቀት አማቂ ጋሶች ልቀታቸውን ለመቀነስ ያሉ አማራጮችን እንዲገነዘቡና በፈቃደኛነት ላይ የተመሰረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ መቀነሻ ዕቅድን ተግባራትና ዒላማዎች ከየከተሞቻቸው የቆሻሻ አስተዳደርና አወጋገድ ዕቅድና ፕሮግራሞች ጋር አጣጥመው ለመተግበር ይረዳቸዋል።

- **ከተሞችና የከተማ ማዕከላት የህግ ማዕቀፎቻቸው በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖን ለማሳካት በሚያስችል መልኩ መከለስ ያስፈልጋቸዋል።** የዚህ ስራ ዓላማ የከተሞችን የቁጥጥር ስርዓት ማሻሻልና ከከተሞች የሚመነጩ ቆሻሻዎችን ለማስተዳደር የሚረዱ የቴክኖሎጂዎችንና አዳዲስ ኢንቨስትመንቶች በዘርፉ የሚፈጠሩበትን ሁኔታ ለማበረታታት ይረዳል።

- **ከተሞች የየራሳቸውን 'በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖ መቀነሻ ዕቅድ በውጤታማነት ሊያስተገብሩ የሚችሉ ተቋማትን ማደራጀት አለባቸው።** ከተሞች ከዘርፉ ጋር የተያያዙ አዳዲስና ፈጠራ የታከለባቸው አማራጮችን ለመሞከር ጥሩ ዕድል አላቸው። ለምሳሌ በከተሞች እንዲተገበሩ የተለያዩ ውጥኖች በቅንጅት ተጣጥመው እንዲተገበሩና የጠነከረ ማህበረሰብ ለመፍጠር የሚያስችል እድል አላቸው። ከዚህ አኳያ ቀልጣፋና ውጤታማ ተቋማዊ አደረጃጀት መፍጠር የከተሞችን የአረንጓዴ ልማትና እድገት ዕቅዶች ስኬት ለማረጋገጥ ይረዳል። በተጨማሪም የከተሞችን የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ለመቀነስና ለአየር ንብረት ለውጥ አይበገሬነት መሳካት የተቀመጡ ዒላማዎችን ለማሳካት ይረዳል።

- **የከተሞችን የደረቅ ቆሻሻ ለመከላከል የሚለዩት አማራጮች ደረቅ ቆሻሻዎችን በመከላከል፣ በመቀነስ፣ መልሶ በመጠቀምና እንደገና አምርቶ በመጠቀም ላይ ያተኮረ መሆን አለበት።** እንደ ሀገር ተመጋጋቢ የሆነ የአመራረት ዘይቤን የሚከተል የኢኮኖሚ ዕድገት ስልትን መከተል ዘርፈ ብዙ የሆኑ አካባቢያዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎች ይኖሩታል። የደረቅ ቆሻሻዎችን በአግባቡ ባለማስተዳደር የተነሳ ከፍተኛ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ይከሰታል። ከደረቅ ቆሻሻዎች የሚወጣ የሙቀት አማቂ ጋዞችን የተመለከቱ ትንበያዎች እንደሚያመለክቱት ለባሳ አፈር (landfill) ከደረቅ ቆሻሻዎች ከሚወጣው የሙቀት አማቂ ጋዞች ትልቁን ድርሻ ያበረክታል። በሌላ መልኩ ደግሞ በተለይም ከፍተኛ የሆነ የተፈጥሮ ምርቶች ውጋጆች (organic) ባሏቸው ሀገራት የተቀናጀ የቆሻሻ አስተዳደርና አወጋገድ ዘዴ የሙቀት አማቂ ጋዞችን ልቀት ለመቀነስ የተሻለ አማራጭ መሆኑን ጥናቶች ያመለክታሉ። በዚህም የተነሳ በደረቅ ቆሻሻዎች አስተዳደር ዘርፍ በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖ መቀነሻ ዕቅድን በውጤታማነት ለማስተግበር፣ በመሠረተ ልማት ላይ መዋለ ንዋይን ማፍሰስና ስራውን የሚደግፉ የተለያዩ የቴክኖሎጂ አማራጮችን በአግባቡ መለየትና በተገቢው የፖሊስ ማዕቀፍ መደገፍን ይጠይቃል።

